# ኖብል ኮሮናቫይረስ

## ኖብል ኮሮናቫይረስ ምንድን ነው?

ኖብል ኮሮናቫይረስ (2019-nCoV) ከዲሴምበር 2019 ጀምሮ በሰዎች ላይ ብቻ የተሰራጨ የቫይረስ ዓይነት ነው። ስለዚህ አዲስ ቫይረስ ያለው መረጃ ጥቂት በመሆኑና በአንዳንድ ሰዎች ላይ ደግሞ ከባድ ሕመምና የሳምባ ምች የማስከተል አቅም ስላለው የጤና ባለሙያዎችን አሳስቧቸዋል።

## ኖብል ኮሮናቫይረስ የሚሰራጨው እንዴት ነው?

የጤና ባለሙያዎች ይህ አዲስ የኮሮና ቫይረስ እንዴት እንደሚሰራጭ ዝርዝር መረጃዎችን ገና እያወቁ ነው። ሌሎች ኮሮና ቫይረሶች ከአንድ ከተጠቃ ሰው ወደ ሌሎች ሊተላለፉ የሚችሉት በሚከተሉት መንገዶች ነው፡-

- በሳል እና ማስነጠስ ወቅት በአየር አማካኝነት
- እንደ የሰውነት ንክኪ ወይም የእጅ መጨባበጥ ባለ የቅርብ የሰውነት ንክኪ
- ቫይረሱ ያለበትን ዕቃ ወይም ገጽታ ከነኩ በኋላ አፍዎትን፣ አፍንጫዎትን ወይም ዓይንዎትን ሲነኩ
- አልፎ አልፎ ደግሞ ከሰገራ ጋር በሚፈጠር ንክኪ አማካይነት

## ኖብል ኮሮናቫይረስ አስከፊነቱ ምን ያህል ነው?

ባለሙያዎች በኮሮና ቫይረስ ምክንያት ስለሚከሰቱ ሕመሞች አሁንም ድረስ አዳዲስ ነገር እያወቁ ነው። ሪፖርት ከተደረጉ ጉዳዮች መካከል ከመጠነኛ ሕመም (ከጉንፋን ጋር ተመሳሳይ የሆነ) ጀምሮ በሆስፒታል ተኝቶ መታከምን እስከሚጠይቅ ከባድ የሳምባ ምች ድረስ ይገኙበታል። እስካሁን ድረስ፣ በቫይረሱ ምክንያት ለሞት የተዳረጉት በዋነኛነት ዕድሜያቸው የገፋና ሌሎች የጤና ችግሮች ያሉባቸው ጐልማሶች ናቸው።

## ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

የኖብል ኮሮና ቫይረስ እንዳለባቸው በምርመራ የተረጋገጠባቸው ሰዎች ለቫይረሱ ከተጋለጡ በኋላ ቢያንስ በ2 ቀናት ውስጥ ወይም ቢበዛ እስከ 14 ቀናት ድረስ ምልክቶች ይታዩባቸዋል።

ትኩሳት



ሳል



ለመተንፈስ መቸገር



## ለኮሮና ቫይረስ የመጋለጥ ስጋት ያለበት ማነው?

በአሁኑ ጊዜ ለጠቅላላው ሕዝብ ያለው የስጋት መጠን ዝቅተኛ ነው። በዚህ ጊዜ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በቫይረሱ የተጠቁ ጥቂት ግለሰቦች አሉ። የመሰራጨት ስጋትን ለመቀነስ፣ የጤና ጉዳይ ሃላፊዎች ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር በትብብር በመስራት ማንኛውንም ተጠርጣሪ ኬዝ በፍጥነት ለመለየትና ለመገምገም ይጥራሉ።

ወደተወሰኑ የዓለም ክፍሎች የሚሄዱና የሚመጡ ተጓዦች ላይ የስጋት መጠኑ የበለጠ ነው። ከ CDC የተላለፈውን የቅርብ ጊዜ የጉዞ መመሪያ ከ wwwnc.cdc.gov/travel ይመልከቱ።

## ራሴን  በኖቭል ኮሮናቫይረስ ከመጠቃት መከላከል የምችለው እንዴት ነው?

ወደ ውጭ ሃገር ጉዞ የሚያደርጉ ከሆነ (ወደ ቻይና ነና ወደለሌሎችም በታዎች ቢሆን) የ CDC መመሪያን ይከተሉ፡- wwwnc.cdc.gov/travel.

በዚህ ሰዓት፣ ኖቭል ኮሮናቫይረስ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በስፋት እየተሰራጨ አይደለም፤ ስለዚህ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ የሚመከሩ ተጨማሪ ቅድመ ጥንቃቄዎች የሉም። ኢንፍሉዌንዛ እና ጉንፋን እንዳይሰራጭ ለመከላከል የሚወስዷቸው እርምጃዎችም ኮሮናቫይረስን ለመከላከል ያግዛሉ፡-



- እጆችዎትን በውሃና ሳሙና ይታጠቡ። ሳሙና ከሌለ፣ የእጅ ማጽጃ ፈሳሽን ይጠቀሙ።
- እጅዎትን ሳይታጠቡ ዓይንዎትን፣ አፍንጫዎትን ወይም አፍዎትን ከመንካት ይቆጠቡ
- ከታመሙ ሰዎች ጋር ንክኪን ያርቁ
- በታመሙ ጊዜ ቤት ውስጥ ይቆዩና ከሌሎች ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪን ያስወግዱ
- ሲያስሉ ወይም ሲያስነጥሱ አፍዎትን/አፍንጫዎትን በሶፍት ወረቀት ወይም በልብስዎ እጅጌ ይሸፍኑ



በአሁኑ ጊዜ፣ የኖቭል ኮሮናቫይረስ ኢንፌክሽኖችን ለመከላከል የሚያስችሉ ክትባቶች  የሉም።

## ኖቭል ኮሮናቫይረስ እንዴት  ይታከማል?

ለኮሮናቫይረስ ተብለው ፈቃድ ያገኙ መድሃኒቶች የሉም። መጠነኛ የኮሮናቫይረስ ሕመም ያለባቸው አብዛኞቹ ሰዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ፈሳሽ በመጠጣት፣ እረፍት በማድረግ፣ የሕመም ማስታገሻና የትኩሳት መከላከያ መድሃኒቶችን በመውሰድ ከሕመሙ ራሳቸው ያገግማሉ። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ሁኔታዎች ህመሙ ወደ ሳምባ ምች እንዲያድግና የሕክምና እንክብካቤ ወይም በሆስፒታል ተኝቶ ሕክምና እንዲያስፈልግ ሊያደርጉ ይችላል።

ለተጨማሪ መረጃ፡- www.clevelandhealth.org

የተሻሻለበት ቀን **2/05/2020 Amharic**



Adapted with permission from Public Health – Seattle & King County